**ፀሐይ ባንክ የክሬዲት ካርድ አገልግሎት በይፋ መስጠት ጀመረ**

ፀሐይ ባንክ የክሬዲት ካርድ አገልግሎት ማስጀመሪያ መርሐግብር በባንኩ ዋና መስሪያ ቤት መስከረም 4 ቀን 2016 ዓ.ም አከናውኗል።

በአገልግሎቱ ይፋዊ ማስጀመሪያ መርሐግብር ላይ ተገኝተው ማብራሪያ የሰጡት የፀሐይ ባንክ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ያሬድ መስፍን፤ በኢትዮጵያ በስፋት ያልተጀመረና ጥቅም ላይ ያልዋለውን የክሬዲት ካርድ አገልግሎት ፀሐይ ባንክ በቀዳሚነት ማስጀመሩን ጠቁመዋል።

ባንኩ አገልግሎቱን የጀመረው በቂ የቴክኖሎጂ ዝግጅት አድርጎ እና አስፈላጊውን የብሔራዊ ባንክ ፈቃድ አግኝቶ መሆኑን ዋና ሥራ አስፈጻሚው ተናግረዋል።

የፀሐይ ክሬዲት ካርድ አገልግሎት ደንበኞች በተፈቀደላቸው የብድር መጠን የብድር ጊዜው እስከሚያበቃ ድረስ እንደፈለጉ መጠቀም የሚያስችል መሆኑንም አቶ ያሬድ ገልጸዋል።

አገልግሎቱ ደንበኞች ለሚገጥማቸው ጊዜያዊ ወይም አስቸኳይ የገንዘብ እጥረት ትልቅ መፍትሔ የሚሰጥ መሆኑን የገለፁት አቶ ያሬድ፤ ደንበኞች ምንም አይነት ማስያዣ ማቅረብ የማያስፈልጋቸው መሆኑን ጠቁመዋል።

ደንበኞች የሚከፍሉት የአገልግሎት ክፍያም እጅግ ተመጣጣኝ እና በተጠቀሙት የገንዘብ መጠን ብቻ መሆኑን ገልጸዋል።

ከዚህ ቀደም በብድር አገልግሎት ማዕቀፍ ውስጥ ያልተካተቱ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለመድረስ አገልግሎቱ ከፍተኛ ዐቅም ይፈጥራልም ብለዋል።

ፀሐይ ባንክ የክሬዲት ካርድ አገልግሎት መስጠት የጀመረው ከባንኩ ጋር የሥራ ግንኙነት ላላቸው ተቋማት ሰራተኞች እና የባንኩ ተቀዳሚ ደንበኞች እንዲሁም ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት ተጠቃሚ ለሆኑ ደንበኞች ነው።

**ፀሐይ ባንክ**

**ለሁሉ!**